207

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# *የ1996 በጀት ዓመት*

# *የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ*

አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1995

6

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# *የ1996 በጀት ዓመት*
# *የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ*

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 1995

# ማውጫ

**አርዕስት** | **ገጽ**


1. መግቢያ ........................................ 1
2. የ1995 የስምንት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ........................ 2
3. የ1996 የሚካሄድ ጥናት የዕቅድ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ስልቶች ......... 7
4. የ1996 ዕቅድ ይዘት ........................................ 8
5. የ1996 ካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ ........................ 8
6. የ1996 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት ........................ 10
7. የ1996 ጥናቶች ግብና መግለጫ ........................................ 17
8. የ1996 የሰው ኃይል ፍላጎት ........................................ 26
9. የ1995 ጥናቶች መርሀ-ግብር ........................................ 26
10. ትኩረትና መመሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ........................ 37

# የ1996 ዓ.ም የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መንግሥት ለሚያወጣቸው ኢኮኖሚያሚና ማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጠቀሜታ ያላቸው የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ሊገልጹ የሚችሉ ወቅታዊ የሆኑ ጥናቶችን በማካሄድ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የያዙ የተለያዩ ሪፖርቶች በማቅረብ ላይ ይገኛል:: እነዚህ የጥናት ሪፖርቶች በየደረጃው የታቀዱ ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችሉ ሲሆን፣ በየዘርፉ ለሚካሄዱ ጥናቶችና ምርምሮችም ጠቀሜታቸው የጎላ ነው::

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የአገሪቱን የስታቲስቲክስ ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት በየጊዜው የተሻሻለ የአሠራር ዘዴዎችን መሠረት አድርጎ በርካታ ጥናቶችን በማካሄድ በየዘርፉ ያለውን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት ጥረት ያደርጋል፣ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል::

በ1996 በጀት ዓመት መ/ቤቱ የመንግሥትን የልማት ትኩረት አቅጣጫና የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት እንዲሁም የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅም በመገምገም የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ ዕቅድ ይዟል:: እነዚህ በዕቅድ የተያዙ ጥናቶች መሠረታዊ የሆኑ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መረጃዎችን የሚያስገኙ ሲሆኑ፣ ውጤታቸውም በየደረጃው ለሚገኙ የስታቲስቲክስ መረጃ ተጠቃሚዎች ወደፊት ለሚያዘጋጇቸው ዕቅዶችና ለሚያከናውኗቸው ምርምሮች በመነሻነትና በማጣቀሻነት እንደሚያገለግሏቸው ይታመናል::

ይህ የ1996 ዓ.ም ዕቅድ በ10 የተለያዩ ክፍሎች የቀረበ ሲሆን፣ በክፍል 1 መግቢያ፣ በክፍል 2 ደግሞ የመ/ቤቱን የ1995 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማን ይዟል:: በክፍል 3 የ1996 ዕቅድ ዓላማዎችና የአፈፃፀም ስልቶችን ለማቅረብ ተሞክሯል:: በክፍል 4 የ1996 ዕቅድ ይዘት የተብራራ ሲሆን፣ በክፍል 5 ደግሞ ለታቀዱት ጥናቶች ማስፈፀሚያ የሚውል የካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ ቀርቧል:: እንደዚሁም ከክፍል 6 እስከ 9 ድረስ የ1996 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት፣ የ1996 የዕቅድ ግብ፣ የሰው ኃይል ፍላጎትና የዕቅዱ መረሃ-ግብር በቅደም ተከተል እንዲካተት ተደርጓል:: በመጨረሻም በክፍል 10 የ1996 ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል::

## 2. የ1995 የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ

### 2.1 ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

በ1995 ዓ.ም በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ሥር ዘጠኝ አዳዲስ ጥናቶችን ለማካሄድ በዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት እስከ የካቲት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ባሉት ስምንት ወራት ውስጥ፡-

#### ሀ/ የግብርናና የተፈጥሮ ሃብትን በተመለከተ

የ1995 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃ ከመስክ ተሰብስቦና በኮምፒውተር ተቀነባብሮ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ እንደዚሁም የግብርና ግብዓቶችና አሠራር ጥናት መረጃው ከመስክ ተሰብስቦ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የመረጃ ቅንብሩ ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

#### ለ/ የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስ ዝግጅትን በተመለከተ

ለ1995 በጀት ዓመት የሚያገለግለው የዋጋ ጥናት መጠይቅ ታትሞ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን፣ መረጃውም ከመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የ11 ክልሎች/ መስተዳድሮች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀው የሸማቶች መመዘኛ ጠቋሚ አሃዞች እስከ ኅዳር ወር 1995 ዓ.ም ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ እስከ ጥር ወር 1995 ዓ.ም ድረስ ያለው ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

#### ሐ/ የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛን በተመለከተ

በበጀት ዓመቱ በዘርፉ ሊጠኑ ከታቀዱት ጥናቶች የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናትና የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት መረጃ ከመስክ የመሰብሰቡ ተግባር ተጠናቋል፡፡ በመሆኑም ለመረጃ ቅንብር ሥራው የኢዲትና ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቶ ስልጠና ለኤዲተሮች ተሰጥቶ የኤዲትና ኮዲንግ ሥራው ለጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናትና ለአነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት ተጀምሯል፡፡

### መ/ <u>የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

በ1993 ዓ.ም ተካሂዶ የነበረውና ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከዓለም ሥራ ድርጅት ጋር በመተባበር የተከናወነው የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናትን በተመለከተ ለመረጃ ተጠቃሚዎች የማማሻ ቀን የማስተዋወቅ ሥራ ተከናውኗል:: በማስተዋወቂያ ሴሚናሩ ላይ ከላይ ከተገለጹት ሁለት መ/ቤቶች በተጨማሪ በሕፃናት ዙርያ የተለያዩ የማህበራዊ ተግባር የሚያከናውኑ ከመንግሥታዊና ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች የተወከሉ ከ120 በላይ ባለሙያዎች ተገኝተዋል::

## 2.2 <u>የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎችን በተመለከተ</u>

በ1994 ዓ.ም ከገጠር የአርሶ አደሩ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ በመስከ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የግብርና ናሙና ቆጠራ ሥራ በ1995 ዓ.ም የመረጃ ቅንብሩና የሪፖርት ዝግጅቱ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል:: በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ውስጥ:-

- የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤት የሆነው የመኸር ወቅት ጊዜያዊ ሰብሎችን በተመለከተ በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና የምርት መጠን (Preliminary Results on Area, Prodiction and Yield of Temporary Crops) የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል::

- የዚሁ ቆጠራ ውጤት የሆነው በቋሚ ሰብሎች የተሸፈነ የመሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና፣ ቬሪፊኬሽን ሥራ ተጠናቆ የቆጠራውን ውጤት የያዙ ሠንጠረዦች የወጡ ሲሆን፣ ሪፖርት የማዘጋጀት ተግባሩም ተጀምሯል::

- የግብርና ናሙና ቆጠራ ውጤትን በየክልሉ ሪፖርት ለማዘጋጀት የመጀመሪያ የሆነው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቆጠራ ውጤት የመኸርና የበልግ እንዲሁም የገጠርና የከተማ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ በጊዜያዊና በቋሚ ሰብሎች መረጃው ተቀንባብሮና ሪፖርቱ ተጠናቆ ለሕትመት በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል::

- የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ አንዱ የሆነው የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ቀደም ብለው በተዘጋጁ የቆጠራውን ውጤት በሚያግዩ

ሠንጠረዦች ላይ ወጥተው የቤንሻንጉል ጉሙዝ የመኸር፣ የበልግ፣ የገጠርና የከተማ መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል።

- የግብርና ናሙና ቆጠራ የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሀብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ ለገጠሩ አካባቢ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል። በመሆኑም የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የትግራይ፣ የአፋር፣ የአማራና የኦሮሚያ ክልል መረጃዎች ተቀነባብረው ውጤቱ በባለሙያዎች በመገምገም ላይ ይገኛል። የቀሪዎቹ ክልሎች የመረጃ ቅንብር፣ የከተማና የሰፋፊ/መካከለኛ/ እርሻዎች መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

- የቆጠራው የመሬት አጠቃቀም መረጃ በኮምፒውተር የማቀነባበር ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ይህን መረጃ በተሻሻለውና የቆጠራውን ውጤት ለማቅረብ በተዘጋጀው ሠንጠረዥ የማዋሃድ ሥራ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መረጃ ላይ እየተካሄደ ነው።

- የግብርና ናሙና ቆጠራ የምርት አጠቃቀም፣ የእርሻ መሣሪያዎችና ማከማቻዎች እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ ተጠናቆ መረጃዎቹን ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ማለትም በአፋር ክልል ሊደረግ ለታቀደው የቤት እንስሳት ቆጠራ የሚውሉ መጠይቆች መመሪያና የኤዲት-ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

## 2.3 የሰው ኃይል ቅጥርና ሥልጠናን በተመለከተ

በ1995 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,513 ቋሚና 2,213 የኮንትራት በጠቅላላው 3,726 ሠራተኞች ነበሩ። በበጀት ዓመቱ ለመቅጠር ከታሰበው ተጨማሪ የሰው ኃይል እስከ የካቲት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ 32 ቋሚና 2,083 የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር ተፈፅሟል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ስምንተኛ ወር መጨረሻ ላይ ከመ/ቤቱ በተለያዩ ምክንያት ሥራቸውን የለቀቁ ሠራተኞችን ሳይጨምር 1,423 ቋሚና 815 ደግሞ የኮንትራት ሠራተኞች በድምሩ 2,238 ሠራተኞች በሥራ ላይ ይገኛሉ።

መ/ቤቱ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማስፈፀም ያሉትን ሠራተኞች በተለያዩ ሙያዎች ማሠልጠን ይጠበቅበታል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ውስጥ በሥልጠናው ዘርፍ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውነዋል።

ሀ. በ1995 የትምህርት ዘመን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተው የማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም እንዲከታተሉ አንድ ሠራተኛ በዲሞግራፊ፣ ሁለት ሠራተኞች በስታቲስቲክስ እና ሦስት ሠራተኞች በኢኮኖሚክስ ትምህርት ዘርፍ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎላቸው ትምህርት ጀምረዋል። እንደዚሁም ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ከቆዩ ሠራተኞች ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ አንድ ሠራተኛ በዲሞግራፊ እንዲሁም አንድ ሠራተኛ በስታቲስቲክስ የማስተርስ ዲግሪ አግኝተው መ/ቤቱን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ከዚህ ሌላ አንድ ሠራተኛ ከሕንድ መንግሥት በተሰጠው የነፃ ትምህርት ዕድል ወደሕንድ ሄዶ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ነው።

ለ. 1995 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ስር ለሚካሄዱ በገጠር የግብርና ናሙና ጥናቶች፣ ለአምራቾች ዋጋ ጥናት፣ ለጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ ለአነስተኛ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ ለመደበኛ ያልሆነ የሥና ዘርፍ ጥናትና ለአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት በዋናው ም/ቤትና በ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለባለሙያዎችና ቀጥታ በሥራው ላይ ለሚሳተፉ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሐ. ለመ/ቤቱ ሠራተኞች አዲስ የወጣውን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በገጠር ልማት፣ በአቅም ግምባታና በዲሞክራሲ ዕንስ ሀሳብ ላይ ተወያይቶ አንድ አገራዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። በዚሁም መሠረት የዋናው መ/ቤት ሠራተኞችን በሁለት በመከፈል ሥልጠናና ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ለ25ቱ ቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች በ8 የሥልጠና ማዕከላት ከላይ በተጠቀሱት ርዕሶች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል።

## 2.4 የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ

በ1995 በጀት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት ግምጃ ቤት ለሁለቱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ በጠቅላላው ብር 33.826.700 የተፈቀደ ሲሆ፣ ይኸውም ብር 19.688.300 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የሚውል፣ ቀሪው ብር

14,138,400 ደግሞ ለግብርና ናሙና ቆጠራ በአርሶ አደሩ አካባቢ የተሰበሰበውን መረጃ ለማቀነባበርና ለሪፖርት ዝግጅት እንደዚሁም በበጀት ዓመቱ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለሚካሄደው የግብርና ቆጠራ ማስፈፀሚያ የሚውል ነው::

ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተፈቀደው በጀት ውስጥ እስከ የካቲት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ብር 15,684,100 ወጪ ተደርጓል:: አፈፃፀሙም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 79.7 በመቶኛ ነው::

ለግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ሥራዎች ከተፈቀደው ብር 14,138,300 ብር ላይ እስከ የካቲት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ብር 1,912,100 ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር 13.5 በመቶ ነው:: ቀሪው ገንዘብ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ሊካሄድ ለታሰበው ዝቅ ብሎ በሚበር የአውሮፕላን ቆጠራና ለተዛማጅ ሥራዎች ይውላል::

## 2.5 በ1995 ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች

ሀ. የመ/ቤቱ የሰው ኃይልና ሎጂስቲክስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየሰፋ ይገኛል:: ሆኖም አሁን የምንጠቀምበት ጽ/ቤት አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ሠራተኞችን ሎጂስቲክስ የመያዝ አቅም ያለው በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የቢሮ ችግር በመኖሩ በሥራችን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሣድሯል::

ለ. መንግሥት ተግባራዊ እንዲሆን ያወጣው የተሽከርካሪዎች ኢንሹራንስ ሽፋን አፈጻጸም የመ/ቤቱን በርካታ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል:: በመሆኑም አነስተኛ ቁጥር ባላቸው (የአገልግሎት ዘመናቸው ከ10 ዓመት በታች በሆኑ) ተሽከርካሪዎች የመስክ ሥራችንን ለመከታተል በመገደዳችን ወቅታዊ የሆነ ቁጥጥር በባለሙያዎች እንዳይካሄድ ችግር አስከትሏል::

ሐ. በሥራ ላይ ያለው የመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር በተወሰነ የሰው ኃይል በተደራጀ አንድ መምሪያ አማካይነት 22 ቅ/ጽ/ቤቶችን ከዋናው መ/ቤት ለመቆጣጠርና ለመምራት እንዲችል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው:: በመሆኑም የመ/ቤቱን ኃላፊዎች ተጨማሪ የሥራ ጫና በሚፈጥር መልኩ ከተሰጣቸው ኃላፊነት ወጪ እንዲሰሩ የሚያስገድድ በመሆኑ በመደበኛ ተግባራቸው ላይ ተፅዕኖ አሣድሯል::

## 3. በ1996 የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማዎችና የአፈፃፀም ስልቶች

### 3.1 በ1996 የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማ

በ1996 የሚካሄዱ ጥናቶች ዕቅድና ዓላማዎች ከመ/ቤቱ አበይት ተግባራት ጋር የተቀናጁ ሆነው የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ።

ሀ. ለፕላን ዝግጅት፣ ለክትትልና ግምገማ፣ ለምርምር፣ ለፖሊሲ ቀየሳና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሊያገለግሉ የሚችሉ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የዲሞግራፊ መረጃዎችን በተቀናጀ አሠራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

ለ. በስታቲስቲክስ ሥራ አኳያ በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝና የሪፖርት ሥርዓት እንዲዘረጋ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

ሐ. ወደፊት የሚኖረውን ሰፊ የስታቲስቲክስ የመረጃ ፍላጎት ከማሟላት አኳያ አመቺና ተስማሚ የሆኑ የስታቲስቲክስ ሥራዎች ማከናወን፣

### 3.2 በ1996 የሚካሄዱ ጥናቶች የአፈፃፀም ስልቶች

ሀ. የአገሪቷ የስታቲስቲክስ ሥራ ጥራትና ደረጃው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይቻል ዘንድ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አቅሙን ለማጎልበት ጥረት ማድረግ፣

ለ. ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት በማጠናከር በተለይም ሕብረተሰቡ የስታቲስቲክስ መረጃ አስፈላጊነትና ጥቅም በሚገባ ተረድቶ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ ትብብር እንዲያደርግ በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተገቢውን ትምህርትና ቅስቀሳ ማድረግ፣

ሐ. የስታቲስቲክስ የአሠራር ዘዴን በማሻሻል የመረጃ መሰብሰብ፣ ቅንብርና ትንተና ሥራ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ስለሚያስፈልግ በዚህ በኩል የሚመደብ ሠራተኛ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እንዲሰለጥን ማድረግ፣

መ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተለያዩ የውጭ አገር መንግሥታት፣ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ሆነ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት

በኩል ግንኙነት በመፍጠርና ብሎም በማጠናከር ጥናት ማካሄድ፣ የሥልጠናና የፋሲሊቲዎች ድጋፍ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ናቸው።

## 4. የ1996 ዕቅድ ይዘት

በ1996 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በዛ ያሉ ጥናቶችን ለማካሄድ መ/ቤቱ በዕቅድ ይዟል። ለዚህም የመ/ቤቱን የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ ሎጂስቲክስና ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚፈቀድለትን የፋይናንስ አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ጥናቶቹን በበጀት ዓመቱ ለማካሄድ ታስቧል። በመሆኑም በ1996 ዓ.ም የሚጠኑ ጥናቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

እነዚህም:-

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /በገጠር/
- የሰብል ምርት ጥናት በመኸርና በበልግ /በገጠር/
- የመሬት አጠቃቀም ጥናት /በገጠር/
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት /በገጠር/
- የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ /Farm Management Practices/ ጥናት /በገጠር/
- የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት /በገጠር/
- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማ/
- የኢኮኖሚ ተቋማት አጠቃላይ ቆጠራ/በከተማ/
- ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት /በከተማ/ Current Employment Survey
- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ሙከራ ጥናት /በከተማ/
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት /በተመረጡ ገበያዎች/

## 5. የ1996 ዓ.ም የካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ

### 5.1 የካፒታል በጀት ፍላጎት

መ/ቤቱ በ1996 ዓ.ም ለሚያካሂዳቸው ጥናቶች ማስፈፀሚያ በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም 32,611,000 ሚሊዮን ብር የሚያስፈልገው ሲሆን፣ ጠቅላላ ወጪውም ከመንግሥት ግምጃ ቤት፣ የሚሸፈን ይሆናል።

## 5.2 የካፒታል በጀት መግለጫ

በበጀት ዓመቱ ለሚጠኑ ጥናቶች የተያዘው በጀት የመንግሥትን የልማት አቅጣጫ ግምት ውስጥ በማስገባትና የመ/ቤቱን የማስፈጸም አቅም ያገናዘበ ሲሆን፣ የበጀት ፍላጎቱ ዝርዝር የተሰላው ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማካተት ነው።

- በበጀት ዓመቱ መረጃ የሚሰበስብባቸው የቆጠራ ቦታዎች በገጠር 2,072 እና በከተማ 790 በድምሩ 2,826 ሲሆኑ፣ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ከየድርጅቶቹ መረጃው ይሰበሰባል።

- የጥናት ሪፖርቶቹ በገጠርና በከተማ በዞን ደረጃ ሪፖርት የሚያወጣላቸው ሲሆኑ፣ እንደ ጥናቶቹ ሁኔታ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃም ሪፖርቶች እንዲወጡ ይደረጋል።

- በደመወዝ የወጪ አርዕስት የተጠቀሰው የሰው ኃይል በሙሉ በኮንትራት ቅጥር የሚሟላ እንጂ መደበኛ ወይም ቋሚ ሠራተኞችን አይጨምርም። ሆኖም የቋሚ ሠራተኞች ወጪ በቁጥጥርና በሥልጠና ወቅት ለሚሳተፉት የሚከፈላቸው የውሎ አበልና እንዳስፈላጊነቱ ለሌሎች ወጪዎች በፕሮጀክቱ ሂሳብ የሚሸፈን ይሆናል።

- ለወጪ ቅነሳና እንዲሁም የሰው ኃይል ጉልበት በአግባቡ ለመጠቀም ኢዲተሮችና የመረጃ ኢንኮደሮች በሚወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት በተናጠል ወይም በጋራ የሁሉንም ጥናቶች መረጃዎች ኢዲትና ኮድ የሚደረጉ ሲሆን፣ መረጃ ኢንኮደሮችም መረጃዎችን ወደ ኮምፒዩተር ውስጥ ያስገባሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም በሥልጠናና በመስክ ቁጥጥር ወቅት ለሁሉም ጥናቶች የመስክ መኪናዎች አጠቃቀም በጋራ ይሆናል። እንደዚሁም ከዋናው መ/ቤት የኢክስፐርት ተቆጣጣሪዎች ስምሪት በቅንጅት ለገጠርና ለከተማ ጥናቶች ይሆናል።

- በጽሕፈት መሣሪያዎችና በሕትመት የወጪ ርዕስ የተገለጸው አኃዝ ለጥናቶቹ የሚያስፈልገውን የሚያጠቃልል ሲሆን በዝርዝር ሲገለጽ ለጥናቶቹ ለሚሰማራው የሰው ኃይል የሚያስፈልገው የጽሕፈት መሣሪያዎች ማለትም እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ላፒስ፣ እስክሪፕቶ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ክላሰር... ወዘተ ሲሆኑ፣ በሕትመት ወጪ የሚጠቃለሉ ደግሞ ለመመሪያዎች፣ ለተለያዩ መጠይቆችና ቅጾች እንደዚሁም ለሪፖርቶች ዝግጅት የሚሆን የወረቀት

ብዛትና ኬሚካሎች የሚገዙበት ዋጋ ተተምኖ የተሰላ ነው። ሌሎች ወጪዎች ደግሞ በበጀት ዓመቱ ከሚካሄዱት ፕሮጀክቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው የቀረቡ ይገኛሉ።

- ከ25 ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል 7ቱ በመንግሥት ቤት በነፃ እንዲሁም 18ቱ በኪራይ ቤቶች አስተዳደርና በግለሰብ ቤት በኪራይ የሚሰሩ ናቸው። በመሆኑም ለዓመቱ የሚያስፈልግ የኪራይ በጀት ፍላጎት እንዲታይ ተገርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ በሚካሄዱ ጥናቶች ላይ ለሚሣተፉ የመስክ ሠራተኞች የሥልጠና አዳራሾች እንዲሁም አብዛኛዎቹ ጽ/ቤቶች የተከራዩት ቢሮ በቂ ባለመሆኑ ያላቸውን ሎጂስቲክስ ለማከማቸት ለአጭር ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ መጋዘኖች ኪራይ ተጠይቆላቸዋል።

- ከዚህ በፊት በተሄዱት የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች በሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ወቅትና በተለያዩ ጊዜያት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሥራ ላይ የሕይወትና የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው በዚሁ ተመክሮ ለመስክ ሥራ ለሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ታምኖበት ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ ሆኖ ተጎጂ ሠራተኞች ተጠቃሚ ሆነዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በመስክ ሥራ የሚሠማሩ ሠራተኞች በሙሉ የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ታስቦ የቀረበ በጀት ነው።

- በመ/ቤቱ የሚሠሩ ባለሙያዎች በመ/ቤቱ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በየጊዜው ያላቸውን ሙያ እንዲያሻሽሉና እንዲያጎለብቱ እንዲሁም ከአዳዲስ አሠራሮች ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ በየጊዜው በአገር ውስጥ በሚገኙ ማሰልጠኛዎች የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ በበጀት ዓመቱ ለሚካሄዱ ስልጠናዎች በጀት ጠይቋል። እነዚህም ስልጠናዎች በተለይም ደግሞ አዲስ በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ ለሚመደቡ የመ/ቤቱ አዲስና ነባር ሠራተኞች ስልጠና ላይ የሚያተኩሩ ይሆናሉ ተብሎ በዕቅዱ ተይዟል።

## 6. የ1996 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት

በ1996 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂደው አንድ ፕሮግራም በጠቅላላው 32,611,000 ሚሊዮን ብር የካፒታል በጀት ጥያቄ የቀረበ ሲሆን፣ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 6.1 ለብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም የበጀት ፍላጎት ማጠቃለያ

6.1.1 ለደመወዝ ____________________ ብር 11,209,500

6.1.2 ለሰው ጉልበት ወጪ ____________________ ብር 1,864,800

6.1.3 ለአበል ____________________ ብር 324,300

- ለበረሃ አበል ______ ብር 324,300
- ለመጠለያ አበል ____ ብር -

6.1.4 ለአላቂ ጽ/መሣሪያ ____________________ ብር 222,500

6.1.5 ለሕትመት ____________________ ብር 225,000

6.1.6 ለነዳጅና ቅባት ____________________ ብር 1,726,500

6.1.7 ለውሎ አበል ____________________ ብር 10,442,800

- ለሥልጠና ________ ብር 2,817,771
- ለመስክ ሥራ ______ ብር 7,625,029

6.1.8 ለትራንስፖርት ክፍያ ____________________ ብር 670,400

- ለተሽከርካሪ ________ ብር 258,430
- ለአውሮፕላን ______ ብር 43,970
- ለበቅሎ __________ ብር 368,000

6.1.9 ለተሽከርካሪ ጥገናና ጎማ ግዢ ____________________ ብር 3,875,000

- ለተሽከርካሪ ጥገና __ ብር 2,753,400
- ለጎማ ግዢ ________ ብር 1,121,600

6.1.10 ለቋሚ ዕቃዎች ጥገና ____________________ ብር 240,000

6.1.11 ለኪራይ ____________________ ብር 265,000

- ለጽ/ቤቶች ኪራይ __ ብር 100,000
- ለአዳራሽ ኪራይ ____ ብር 165,000

6.1.12 ለኢንሹራንስ ____________________ ብር 982,200

- ለተሽከርካሪዎች ____ ብር 396,000
- ለመስክ ሠራተኞች __ ብር 586,200

6.1.13 ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ____________________ ብር 75,000

6.1.14 ለስልክ አገልግሎት ክፍያ ____________________ ብር 360,000

6.1.15 ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ____________________ ብር 78,000

6.1.16 ለአገር ውስጥ ሥልጠና ____________________ ብር 50,000

ድምር ____________________ ብር 32,611,000

| የስራ ዓይነት/ በበጀት ርዕስ | ገጠር | | | | ከተማ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | ዋጋ | ወር | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ወር | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ወር | ድምር |
| 4. የጽ/መሣሪያ | | | | | | | | | | | | |
| . ዋናው መ/ቤት | | | | 132,500 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ቅ/ጽ/ቤቶች | 25 | 300 | 12 | 90,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **222,500** | | | | | | | | |
| 5. ለሕትመት | | | | | | | | | | | | |
| . ለኬሚካልና ቀለም | | | | 225,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **225,000** | | | | | | | | |
| 6. ለነዳጅና ቅባት | | ኪ.ሜ ዓመት | ኪ.ሜ ዋጋ | | | ኪ.ሜ ዓመት | ኪ.ሜ ዋጋ | | | ኪ.ሜ ዓመት | ኪ.ሜ ዋጋ | |
| ሀ. ለስልጠና | | | | | | | | | | | | |
| . በዋናው መ/ቤት | 3 | 1,700 | 0.7 | 3,570 | 3 | 1,200 | 0.7 | 2,520 | 3 | 1,200 | 0.7 | 2,520 |
| . በቅ/ጽ/ቤቶች | 24 | 3,000 | 0.7 | 50,400 | 24 | 3,000 | 0.7 | 50,400 | | | | |
| ለ. ለመስክ ሥራ | | | | | | | | | | | | |
| . በዋናው መ/ቤት | 15 | 3,000 | 0.7 | 31,500 | 15 | 1,500 | 0.7 | 15,750 | 15 | 1,500 | 0.7 | 15,750 |
| . በቅ/ጽ/ቤቶች | 185 | 8,000 | 0.7 | 1,036,000 | 185 | 2,000 | 0.7 | 259,000 | 185 | 2,000 | 0.7 | 259,000 |
| ንዑስ ድምር | | | | **1,121,470** | | | | **327,670** | | | | **277,270** |
| **7. ለውሎ አበል** | **ብዛት** | **ቀን** | **አበል** | **ድምር** | **ብዛት** | **ቀን** | **አበል** | **ድምር** | **ብዛት** | **ቀን** | **አበል** | **ድምር** |
| **7.1 ለስልጠና በዋናው መ/ቤት** | | | | | | | | | | | | |
| **ሀ. በግብርና ስታቲስቲክስ** | | | | | | | | | | | | |
| . በቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | 50 | 15 | 70 | 52,500 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከኃላፊዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 25 | 15 | 47 | 17,625 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚመደቡ አሰልጣኞች | 10 | 10 | 24 | 2,400 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከዋናው መ/ቤት ለተመረጡ ሰልጣኞች | 40 | 10 | 24 | 9,600 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| **ለ. የቤተሰብ በጀት ስታቲስቲክስ** | | | | | | | | | | | | |
| . በቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | 50 | 2 | 70 | 7,000 | | | | | 50 | 2 | 70 | 7,000 |
| . ከኃላፊዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 25 | 2 | 47 | 2,350 | | | | | 25 | 2 | 47 | 2,350 |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚመደቡ አሰልጣኞች | 4 | 2 | 24 | 192 | | | | | 5 | 2 | 24 | 240 |
| **ሐ. የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ** | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት አሠልጣኞች | - | - | - | - | 6 | 7 | 24 | 1,008 | 50 | 3 | 24 | 3,600 |
| . በቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | - | - | - | - | 24 | 12 | 58 | 16,704 | 50 | 7 | 70 | 24,500 |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች /አዲስ አበባ/ | - | - | - | - | 80 | 7 | 18 | 10,080 | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች / አዲስ አበባ/ | - | - | - | - | 17 | 7 | 21 | 2,499 | - | - | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች /ከአዲስ አበባ ዉጪ | - | - | - | - | 40 | 12 | 47 | 22,560 | - | - | - | - |
| **መ. ማህበራዊ ስታቲስቲክስ** | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት አሠልጣኞች | - | - | - | - | 7 | 5 | 24 | 840 | - | - | - | - |
| . ከዋናው መ/ቤት ለተመረጡ ሠልጣኞች | - | - | - | - | 16 | 5 | 24 | 1,920 | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤቶች ለተመረጡ ሠልጣኞች | - | - | - | - | 22 | 9 | 58 | 11,484 | - | - | - | - |

| የስራ ዓይነት/ በበጀት ርዕስ | ገጠር | | | | ከተማ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | ቀን | አበል | ድምር | ብዛት | ቀን | አበል | ድምር | ብዛት | ቀን | አበል | ድምር |
| 7.1 በቅ/ጽ/ቤት ለሚሰጥ ሥልጠና | | | | | | | | | | | | |
| ሀ. በግብርና ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት አሠልጣኞች | 50 | 20 | 70 | 70,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከአሰልጣኞች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 15 | 20 | 47 | 14,100 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤቶች ለተመረጡ ሠልጣኞች | 50 | 17 | 21 | 17,850 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 1,683 | 15 | 47 | 1,186,515 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 496 | 20 | 47 | 466,240 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 196 | 17 | 21 | 69,972 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 219 | 17 | 15 | 55,845 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ለ. የቤተሰብ በጀት ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 490 | 2 | 47 | 46,060 | - | - | - | - | 119 | 4 | 47 | 22,372 |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 90 | 2 | 58 | 10,440 | - | - | - | - | 25 | 2 | 58 | 2,900 |
| ሐ. የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት አሠልጣኞች | - | - | - | - | - | - | - | - | 50 | 9 | 70 | 31,500 |
| . ከአሰልጣኞች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | - | - | - | - | 15 | 9 | 47 | 6,345 |
| . ከቅ/ጽ/ቤቶች ለተመረጡ አሠልጣኞች | - | - | - | - | - | - | - | - | 50 | 5 | 21 | 5,250 |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | - | - | - | - | - | - | - | - | 2,250 | 7 | 20 | 315,000 |
| . ለተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | - | - | - | - | 415 | 7 | 58 | 168,490 |
| መ. ማህበራዊ ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት አሠልጣኞች | - | - | - | - | 25 | 14 | 70 | 24,500 | - | - | - | - |
| . ከአሠልጣኞ ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | 15 | 14 | 47 | 9,870 | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ለተመረጡ አሰልጣኞች | - | - | - | - | 22 | 8 | 21 | 3,696 | - | - | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | - | - | - | - | 200 | 14 | 20 | 56,000 | - | - | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በስምሪት ወቅት | - | - | - | - | 86 | 7 | 47 | 28,294 | | | | |
| . ለተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | 60 | 8 | 21 | 10,080 | - | - | - | - |
| 7.2. ለመስክ ቁጥጥር | | | | | | | | | | | | |
| ሀ. ለግብርና ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ለሚሰማሩ ባለሙያዎች | 50 | 45 | 70 | 157,500 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 15 | 45 | 47 | 31,725 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | 75 | 90 | 70 | 472,500 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከኃላፊዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 25 | 90 | 47 | 105,750 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 415 | 150 | 58 | 3,610,500 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ከተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 115 | 150 | 47 | 810,750 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በስምሪት ወቅት | 2072 | 2 | 47 | 194,768 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ለ. የቤተሰብ በጀት ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ለሚሰማሩ ባለሙያዎች | 30 | 25 | 70 | 52,500 | - | - | - | - | 30 | 25 | 70 | 52,500 |
| . ከባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 15 | 25 | 47 | 17,625 | - | - | - | - | 15 | 25 | 47 | 17,625 |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 100 | 48 | 58 | 278,400 | - | - | - | - | 33 | 72 | 58 | 137,808 |
| . ከተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | 50 | 48 | 47 | 112,800 | - | - | - | - | 25 | 72 | 47 | 84,600 |
| . መረጃ ወደ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች ማድረስ | 13 | 48 | 58 | 36,192 | - | - | - | - | 13 | 48 | 58 | 36,192 |

| | ገጠር | | | | ከተማ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስራ ዓይነት/ በበጀት ርዕስ | ብዛት | ቀን | አበል | ድምር | ብዛት | ቀን | አበል | ድምር | ብዛት | ቀን | አበል | ድምር |
| ሐ. የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ባለሙያዎች | - | - | - | - | 2 | 40 | 70 | 5,600 | 25 | 10 | 70 | 17,500 |
| . ከባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | 2 | 40 | 47 | 3,760 | 15 | 10 | 47 | 7,050 |
| . ለ/አ/አ መረጃ ሰብሳቢዎች ምግና ትራንስ. | - | - | - | - | 75 | 50 | 18 | 67,500 | - | - | - | - |
| . ለአ/አ ተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | 18 | 50 | 21 | 18,900 | - | - | - | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤት መረጃ ሰብሳቢዎች | - | - | - | - | 40 | 50 | 18 | 36,000 | 450 | 20 | 47 | 423,000 |
| . ለቅ/ጽ/ቤት ተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | 25 | 50 | 21 | 26,250 | 250 | 25 | 58 | 362,500 |
| . ከተቆጣጣሪዎች ጋር የሚመደቡ ሾፌሮች | - | - | - | - | 12 | 50 | 18 | 10,800 | 125 | 25 | 47 | 146,875 |
| . ከቅ/ጽ/ቤት የሚመደቡ ባለሙያዎች | - | - | - | - | - | - | - | - | 30 | 20 | 58 | 34,800 |
| . ከባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | - | - | - | - | 25 | 20 | 47 | 23,500 |
| መ. ማህበራዊ ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ባለሙያዎች | - | - | - | - | 25 | 14 | 70 | 24,500 | - | - | - | - |
| . ከባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | 15 | 14 | 47 | 9,870 | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ለሚመደቡ ባለሙያዎች | - | - | - | - | 25 | 16 | 70 | 28,000 | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ለሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | 25 | 16 | 47 | 18,800 | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | 60 | 28 | 58 | 97,440 | - | - | - | - |
| . ከተቆጣጣሪዎች ጋር የሚመደቡ ሹፌሮች | - | - | - | - | 40 | 28 | 47 | 52,640 | - | - | - | - |
| ለቅ/ጽ/ቤት ለሚሰጥ አበል | | | | | | | | | | | | |
| . መለስተኛ ሂሳብ ሰራተኛ (ቅ/ጽ/ቤት) | 25 | 60 | 58 | 87,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ንብረት ክፍል ሠራተኛ ቅ/ጽ/ቤት | 25 | 60 | 47 | 70,500 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | 7,909,726 | | | | 599,595 | | | | 1,933,497 |
| 8. ለትራንስፖርት ክፍያ | ብዛት | ዋጋ | ምልልስ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ምልልስ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ምልልስ | ድምር |
| ሀ. በግብርና ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በስምሪት ወቅት | 2,072 | 30 | 1 | 62,160 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 415 | 30 | 1 | 12,450 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች የበቅሎ ኪራይ | 368 | 100 | 10 | 368,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለዋናው መ/ቤት ባለሙያዎች የአየር ትኬት | 10 | 400 | 6 | 24,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለአውቶብስ ትኬት | 10 | 200 | 1 | 2,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ለ. የቤተሰብ በጀት ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | - | - | - | - | - | - | - | - | 119 | 30 | 2 | 7,140 |
| ሐ. የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ባለሙያዎች የአየር ትኬት | - | - | - | - | 10 | 1,000 | 1 | 10,000 | 10 | 1,000 | 1 | 10,000 |
| . ለአውቶብስ ትኬት | - | - | - | - | 20 | 100 | 1 | 2,000 | 25 | 100 | 1 | 2,500 |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በስምሪት ወቅት | - | - | - | - | - | - | - | - | 1,800 | 50 | 1 | 90,000 |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በመስክ ሥራ | - | - | - | - | - | - | - | - | 450 | 50 | 1 | 22,500 |
| . ለተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | - | - | - | - | 250 | 100 | 1 | 25,000 |
| መ. ማህበራዊ ስታቲስቲክስ | | | | | | | | | | | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በስምሪት ወቅት | - | - | - | - | 200 | 30 | 2 | 12,000 | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች | - | - | - | - | 60 | 30 | 2 | 3,600 | - | - | - | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ለሚመጡ ሰልጣኞች | - | - | - | - | 25 | 70 | 4 | 7,000 | - | - | - | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች ትራንስፖርት | - | - | - | - | 60 | 6 | 28 | 10,080 | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | 468,610 | | | | 44,680 | | | | 157,140 |

| የስራ ዓይነት/ በበጀት ርዕስ | ገጠር | | | | ከተማ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር |
| 9. ለትራንስፖርት ጥገና | | | | | | | | | | | | |
| . ለተሽከርካሪ ጥገና | 200 | 1,377 | 10 | 2,754,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለተሽከርካሪ ጎማ | 200 | 701 | 8 | 1,121,600 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **3,875,600** | | | | | | | | |
| 10. ለመሣሪያ ጥገና | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት | | | | 180,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤት | 25 | 200 | 12 | 60,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **240,000** | | | | | | | | |
| 11. ለቢሮና የሥልጠና አዳራሽ ኪራይ | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር |
| . ለዋናው መ/ቤት | | | | 15,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለ18 ቅ/ጽ/ቤቶች ቢሮ ኪራይ | 18 | 463 | 12 | 100,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለ25 ቅ/ጽ/ቤቶች የሥልጠና አዳራሽ ኪራይ | 25 | 1,200 | 5 | 150,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **265,000** | | | | | | | | |
| 12. ለኢንሹራንስ | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር |
| . በግብርና ስታቲስቲክስ | 2,219 | 213 | 1 | 472,647 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . የቤተሰብ በጀት ስታቲስቲክስ | - | - | - | - | - | - | - | - | 119 | 213 | 1 | 25,347 |
| . የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ | - | - | - | - | 122 | 213 | 0.33 | 8,662 | 2,363 | 213 | 0.13 | 65,431 |
| . ማህበራዊ ስታቲስቲክስ | - | - | - | - | 200 | 213 | 0.33 | 14,200 | - | - | - | - |
| . ለተሽከርካሪ | 200 | 1,980 | 1 | 396,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **868,647** | | | | **22,862** | | | | **90,778** |
| 13. ለኤሌትሪክ አገልግሎት ክፍያ | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25 | 250 | 12 | 75,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **75,000** | | | | | | | | |
| 14. ለስልክ አገልግሎት ክፍያ | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር |
| . ለዋናው መ/ቤት | 1 | 10,000 | 12 | 120,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25 | 800 | 12 | 240,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **360,000** | | | | | | | | |
| 15. ለፖስታ ውሃና ሌሎች አገል.ክፍያ | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር | ብዛት | ዋጋ | ጊዜ | ድምር |
| . ለዋናው መ/ቤት | 1 | 1,500 | 12 | 18,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25 | 200 | 12 | 60,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **78,000** | | | | | | | | |
| 16. ለሰው ኃይል ስልጠና | | | | | | | | | | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት | | | | 50,000 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| ንዑስ ድምር | | | | **50,000** | | | | | | | | |
| ድምር | | | | **26,446,729** | | | | **1,309,774** | | | | **4,855,019** |
| ጠቅላላ ድምር | | | | **32,611,522** | | | | | | | | |

## 7. የ1996 ጥናቶች ግብና መግለጫ

### 7.1 የጥናቶች ግብ

በ1996 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም አሥራ ሶስት የተለያዩ ጥናቶችን በአገሪቱ ገጠርና ከተማ በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ላይ ለማካሄድ ታቅዷል:: በዚህ ፕሮግራም አማካይነት የሰው ኃይል፣ ሎጂስቲክስና በጀትን በማጠናጀት ከሚካሄዱት ጥናቶች መካከል የዋጋ ጥናት ብቻ ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት ተሸጋግሮ የመረጃ ቅንብሩ ሥራ የሚከናወን ሲሆን፣ ሌሎቹን ጥናቶች ግን በተያዘላቸው ዕቅድና መረሃ ግብር መሠረት የሚጠናቀቁ ይሆናሉ::

### 7.2 የጥናቶች ዝርዝር መግለጫ

#### 7.2.1 የግብርና ስታቲስቲክስ ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

ሀ. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት

የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ዓላማዎች

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከነሐሴ 27 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት የአገሪቱ ክልሎች በሙሉ በሚሸፍን መልኩና በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች በገጠር የሚካሄድ ሲሆን፣ የጥናቱም ዓላማዎች፣

- በምርት ዘመኑ ሲገኝ የሚችለውን ምርት ሣይንሣዊ በሆነ መንገድ በመገምገምና በምርት ዘመኑ ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ የጊዜያዊ ሰብል ምርት መጠን ከመኸር ወቅት በፊት በመገመት በዋናው መኸር ወቅት በአገሪቱ ሊመረት የሚችለውን የጊዜያዊ ሰብል ምረት መጠን አስቀድሞ ለመተንበይ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እና

- በምርት ዘመኑ ትርፍ ሊያመርቱ የሚችሉትንና የምርት እጥረት ሊያጥማቸው የሚችሉትን ክልሎችና ዞኖች መለየት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ናቸው::

በሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣

- የሚጠበቀው የምርታማነት ለውጥ ከ1995 ዓ.ም ምርት በሰብል ዓይነት ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር፣ እና
- ለምርታማነት መቀነስ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

ለ. <u>የግብርና ናሙና ጥናት</u>

<u>የግብርና ናሙና ጥናት ዓላማዎች</u>

- በሀገሪቱ በ1996 ሰብል ዘመን የተመረተው ጠቅላላ የሰብል ምርት መጠን (ጊዜያዊና ቋሚ ሰብሎችን) በሰብል ዓይነት ለማወቅ፣ በክልሎችና በዞኖች ደረጃ ያለውን የምርት ሁኔታ ለማወቅ፣ ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፤

- ከአንድ ሄክታር በሰብል የተያዘ መሬት ላይ የሚገኘውን ምርትና ምርታማነት ምን ያህል እንደሆነ እንደዚሁም በክልሎችና በዞኖች መካከል ያለውን ምርትና ምርታማነትን ለማወዳደር የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት፤

- በ1996 ሰብል ዘመን በሀገር ደረጃ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን በዋናው መኸርና በበልግ በመለየት በሰብል ዓይነት ከ1995 ሰብል ዘመን ሁኔታ ጋር ሲወዳደር የታየውን ለውጥ ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎች ለማግኘት፤

- በ1996 ሰብል ዘመን በዋናው መኸርና በበልግ ወቅቶች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ዓይነትና መጠን፣ የምርጥ ዘርና ፀረ ሰብል መድኃኒት ዓይነትና መጠን፣ እንደዚሁም የመስኖ አጠቃቀም… ወዘተ ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፤

- በሀገሪቱ በገጠር በ1996 ሰብል ዘመን ያለውን የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ ማለትም በሰብል የተያዘ መሬት፣ እጻሪ መሬት፣ በግጦሽ የተያዘ መሬት፣ በደን የተሸፈነ መሬት፣ ወዘተ ስፋትና የግብርና ቤተሰቦችና ባለይዞታዎች ብዛትና ሥርጭትን ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት፤

- በ1996 ዓ.ም በሀገሪቱ ያለውን የቤት እንስሳትን በተመለከተ ብዛታቸውን በዓይነት፣ በፆታና በዕድሜ እንደዚሁም በሚሰጡት አገልገሎት ዓይነት ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፣ እና

- ሌሎች ተዛማጅ የግብርናና የዲሞግራፊያዊ ባህርያትን የሚገልጹ መረጃዎች ለማግኘት።

<u>በግብርና ናሙና ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

- የግብርና ቤተሰብ አባላት (ባለይዞታዎች ጨምሮ) ዲሞግራፊያዊ ባህርያቸ፣
- የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ በዋናው መኸርና በበልግ ወቅት፣
  - ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ዓይነትና መጠን በሰብል ዓይነት፣
  - ጥቅም ላይ የዋለ የዘር መጠንና ዋጋ በዘር ዓይነት፣
  - በመስኖ ውሃ የለማ የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣
  - የፀረ ሰብል መድኃኒት አጠቃቀምና ዓይነት፣
  - የሰብል መበላሸት ምክንያትና የብልሽቱ መጠን፣
  - የእያንዳንዱ ሄክታር አማካይ የምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣
  - የመሬት አጠቃቀም መረጃ
    - በሰብል የተያዘ መሬት ስፋት
    - በእዳሪ የተያዘ መሬት ስፋት
    - በግጦሽ የተያዘ መሬት ስፋት
    - በደን የተያዘ መሬት ስፋት
    - በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ መሬት ስፋት
  - የቤት እንስሳት፣ ዶሮ ሀብት ብዛት በዓይነት፣ በዕድሜ፣ በፆታና በሚሰጡት የጥቅም ዓይነት፣
  - የንብ ቀፎዎች ብዛትና ዓየነት እንዲሁም የማር ምርት መጠን፣

### 7.2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

#### ሀ. የአምራቾች ዋጋ ጥናት

የአምራቾች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ አበይት ዓላማዎች፡

- ፖሊሲ አውጪዎች ስለእርሻ ውጤቶች ምርትና ሥርጭት አስመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚረዱ መረጃዎች፡
- ገበሬዎች በአምራቾች ደረጃ ለእርሻ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ መጠን ለማጥናት መሠረት የሆኑ መረጃዎች፡
- የምርት ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎች፡
- የእርሻ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋን የምርት መጠን መመዘኛ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው።

በአምራቾች ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

ለአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የግብርና ውጤቾች የአምራች ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የእህል፡ የጥራጥሬ፡ የቅባት እህሎች፡ የአትክልትና ፍራፍሬ፡ የቅመማቅመም፡ የወተትና የወተት ተዋፅኦ፡ እንቁላል፡ የቁም ከብቶች፡... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

#### ለ. የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ የሚገኙ 120 ትላልቅ ገበያዎች የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማዎች:-

- የችርቻሮ ዋጋ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ፡
- በተለያዩ የሥርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማወቅ፡
- በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለመገምገም፡
- ለቤተሰብ ፍጆታ የዋሉትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ለመተመን፡

- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ምርትና ስርጭት በሚመለከት ፓሊሲ አውጪዎች ውሳኔ ለመድረስ የሚያስችሉ መነሻ መረጃዎች ለማግኘት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት እንደዚሁም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው፡፡

በችርቻሮ ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት፡-

ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ ከተመረጡ ትላልቅ ገበያዎች / በዋና ዋና የመገበያያ ሥፍራዎች /የእርሻና የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከግል ነጋዴዎች የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የልብስ፣ የጫማ፣ የሕንፃ መሣሪዎች፣ የቤት ኪራይ፣ የቤት መገልገያ ዕቃዎች፣ የሕክምና መድኃኒት፣ የመጓጓዣ፣ የትምህርት፣ የመዝናኛ፣ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የሆቴል ምግብና አልጋ፣... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ናቸው፡፡

### 7.2.3 የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

#### ሀ. የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎት ጥናት

በዚህ ጥናት አሥርና ከአሥር በላይ ሠራተኞች ከሚያሰማሩ፣ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ካላቸው፣ አብዛኛው ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ከሚያመርቱ ፋብሪካዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን ጥናቱ የሚካሄደውም በከተማዎች ክልል ነው፡፡

የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ዓላማ፣

- የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፓሊሲና የልማት ዕቅድ አውጪዎች እንደዚሁም ተመራማሪዎች በመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃ በኢንዱስትሪና በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

- ዘርፉ ያስማራውን የሰው ኃይልና የምርት መጠን ለማወቅና ለሀገር ሀብት ውጤት የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት፣

- ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናው ጋር ያለውን መስተጋብር እንዲሁም ከውጭ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በኩል ያለውን ድርሻ ለመገመት የሚያስችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በዝርዝር መሰብሰብ ናቸው::

<u>ከትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

- የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም፣
- የተከፈለ ካፒታል መጠን ( Paid -up - Capital)፣
- የሠራተኞች ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ፣
- የምርት መጠንና ዋጋ፣
- የጥሬ ዕቃ ፍጆታ፣
- ልዩ ከማምረት ይዘት ጋር የተዛመዱና ያልተዛመዱ ወጪዎች፣
- የቋሚ ንብረት ዓይነትና በቋሚ ንብረት ላይ የተደረገ የመዋዕለ ንዋይ መጠን፣
- የማምረት ችሎታ፣ ... ወዘተ አመልካች መረጃዎችን ይሰበስባሉ::

ለ. <u>የኢኮኖሚ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ</u>
<u>የቆጠራው ዓላማዎች</u>

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢኮኖሚው ዘርፍ ፈቃድ ይዘው የተሰማሩ ድርጅቶችን አስመልክቶ አጠቃላይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

- ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶችና አጠቃላይ ቆጠራዎች ለፍሬምነት የሚያገለግል መረጃ ለማስገኘት፣

- የአገሪቱን የኢኮኖሚ ድርጅቶች አስመልክቶ የመረጃ ክምችት /Data Base/ መፍጠር፣

- ለወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጥናቶች /Current Business Survey/ የናሙና መሠረት ለማስገኘት፣ እና

- የአገሪቱን የኢኮኖሚ ድርጅቶች ዕድገትና ሥርጭት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማስገኘት ናቸው።

<u>የኢኮኖሚ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ የሚሰበሰቡ ይመረጃ ዓይነቶች</u>

- በግብርና፣ በማምረቻና በኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ፣ በኮንስትራክሽን፣ በማዕድንና ቁፋሮ፣ በአከፋፋይ ንግድ፣ በውጭ ንግድና በአገልግሎት ንግድ የተሰማሩ ድርጅቶችን በስምና በአድራሻቸው እንዲሁም የኢንዱስትሪ ዓይነት በዝርዝር ማግኘት /By type of defailed economic activities/፣

- የድርጅቶችን አቅም /Size of Establishment/ በሰው ኃይል፣ በካፒታልና በዓመታዊ የሽያጭ /ገቢ/ መጠን በዝርዝር ማግኘት ናቸው።

ሐ. <u>የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ የሙከራ ጥናት/ በከተማ/</u>
<u>የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች</u>

ጥናቱ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በሙሉ /ትላልቅና መካከለኛ/ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

- ፖሊሲ አውጪዎች ስለኢንዱስትሪ ውጤቶች ምርትና ስርጭት ለሚወስዱት ውሣኔ እንዲረዳ፣
- ባለፋብሪካዎች በአምራች ደረጃ ለኢንዱስትሪ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን የዋጋ መጠን ለማጥናት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሃብት ውጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆን መረጃ ለማግኘት፣
- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማጥናት፣
- የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት እንዲያገለግል ነው።

የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የአምራቾች ሙሉ አድራሻ በየከተማው፣
- ምርታቸው የሚሸጡበት አድራሻ፣
- የዕቃዎች ዓይነት መለየት (Item Sepcification) እና፣

  የዕቃዎች ዋጋ ናቸው።

7.2.4 የማሕበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች

ሀ. ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት

ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት ዓላማዎች

- የሀገሪቱን የሰው ኃይል አቅርቦት መጠኝ፣ ጥቅም ላይ ሊውል ከሚችለው የሰው ኃይል ምን ያህሉ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት እገዛ እያደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ምን ያህሉ ጥቅም ላይ ሳይውል እየባከነ እንደሆነ ሊጠቁም የሚችሉ መረጃዎችን በተከታታይነት ለማስገኘት፣ ለውጡን ለመከታተል፣

- በወቅቱ ሥራ የሌላቸው ሰዎችን (Unemployed Population) እንዲሁም ስራ ያላቸው (Employed population) መጠኝ፣ ባህርያቸው ለውጡን በጊዜ ሂደት የሚያሳይ መረጃ ለማስገኘት፣

- የተለያዩ የመንግስትና የግል የኢኮኖሚ አውታሮች ምን ያህል ሰው ሲያሳትፉ እንደሚችሉ በተከታታይነት ለመገምገም፣

- በሥራ ሊሠማራ ስለሚችለው የሰው ኃይል ዋና ዋና የዲሞግራፊያዊና የማህበራዊ ባህርያት መረጃዎችን በተከታታይነት በተጓዳኝ ለማስገኘት፣

- የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ሥምሪት አቅጣጫ ብቃት በቀጣይነት (Macro Economic Monitoring) ሊጠቀሙ የሚችሉ ተከታታይ የሥራ ሁኔታ መረጃዎችን ለማስገኘት፣

- ለሥራ የደረሰውን የሰው ኃይል በሥራ ለማሰማራት የሚያስችሉ ዕቅዶችን ፕሮግራሞችንና ስልቶችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ተከታታይነት ያላቸውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማስገኘት፣
- በዋናው ጥናት (Occasional Labor Force Survey) ላይ የማይገኙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለምሳሌ /ጥናቱን በከተማ ደረጃ ማቅረብን ይመለከታል/

## በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የዲሞግራፊያዊ መረጃዎች ( ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃና የሙያ ዓይነት እና ፍልሰት ሁኔታ)
- የሥራ ስምሪት ሁኔታ (Engagement in Employment)
- በምርታማ ሥራ ስለመሰማራት(Engagement in Productive Activity)
- በምርታማነት ሥራ የሰተሰማሩት በሚመለከት (Employment)
  - የተሰማሩበት ዋነኛ የሥራ መስክ /ዓይነት/
  - በዋነኛነት የሰተማሩበት ድርጅት፣ ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት፣
  - በዋነኛነት በተሰማበት የሥራ መስክ የቅጥር ሁኔታ፣
  - በጠቅላላው በሁሉም ሥራዎች የሰሩት የሥራ ሰዓት መጠኝ
- በከፊል ሠራተኛነት (Under employment)
  - በጠቅላላው የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን በቂ ስለመሆኑ፣
  - በቂ ካልሆነ በተጨማሪ ለመስራት ያላቸው የፍላጎት መጠኝ
  - የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን በቂ ያልሆነበት ምክንያት፣
  - በተጨማሪ በምን ሥራ መሰማራት እንደሚፈልጉ፣
  - በተጨማሪ ለምን ያህል ሰዓት መሥራት እንደፈለጉ፣
  - በተጨማሪ መሥራት የፈለጉበት ዋናው ምክንያት፣
- በምርታማ ሥራ ያልተሰማሩትን ሥራ አጦች በሚመለከት (Unemployment)
  - በምርታማነት ሥራ ያልተሰማሩበት ምክንያት፣
  - ከዚህ ቀደም ሥራ ሰርተው ያውቁ እንደነበረ፣
  - ከነበረ የመጨረሻው የሥራ ዓይነት፣
  - ከመቼ ጀምሮ ሥራውን መሥራት እንዳቆሙ፣
  - ለምን የቀድሞውን ሥራ መሥራት እንዳቆሙ፣
  - አሁን ሥራ በመፈለግ ላይ ስለመሆናቸው፣
  - በምን መንገድ ሥራ እየፈለጉ እንደሆነ፣
  - ለምን ያህል ጊዜ ሥራ እንደፈለጉ፣
  - እስካሁን ያላገኙበት ምክንያት፣
  - ምን ዓይነት ሥራ እንደሚፈልጉ፣

## 8. የ1996 የሰው ኃይል ፍላጎት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1996 በጀት ዓመት የሚያከናውናቸውን ጥናቶች ተግባራዊ ማድረግ 1,450 ከሚጠጉ ቋሚ ሠራተኞች በተጨማሪ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል 12,218 ሲሆን፡ ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

የ1966 የሰው ኃይል ፍላጎት

| ተ.ቁ | የሠራተኛው ሁኔታ | የሰው ኃይል ፍላጎት | |
|---|---|---|---|
| 1 | በሙያ ዓይነት | | |
| 1.1 | የሰለጠነ | 3 | ለ 12 ወራት |
| 1.2 | በከፊል የሰለጠነ | 2,311 | ለ 12 ወራት |
| 1.3 | " " | 280 | ለ 2 ወራት |
| 1.4 | " " | 2,250 | ለ 1.5 ወራት |
| 1.5 | ያልሰለጠነ | 139 | ለ 12 ወራት |
| 1.6 | " " | 4,924 | ለ 2 ወራት |
| | ድምር | 12,218 | |
| 2 | በቅጥር ዓይነት | | |
| 2.1 | ቋሚ | - | |
| 2.2 | ኮንትራት | 7,155 | |
| 2.3 | ጊዜያዊ | 5,063 | |
| | ድምር | 12,218 | |

## 9. የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር

ጥናቶች በአንድ ወቅት ተጀምረው በተወሰነ የጊዜ ግደብ ውስሥ መጠናቀቅ ስላለባቸው መከናወን የሚገባቸው ዝርዝር ተግባራት በወቅቱ እንዲከናወኑና የሥራው እንቅስቃሴ የደረሰበትን ደረጃ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ የድርጊት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት አስፈላጊና ወሣኝ ነው። በመሆኑም የ1996 በጀት ዓመት ጥናቶች አፈፃፀም ወርሃዊ የሥራ መርሃ-ግብር እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።

# <u>የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር</u>

ሠንጠረዥ 3

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚጀመርበት | ሥራው የሚጠናቀቅበት |
|---|---|---|---|
| 1 | <u>የሰብል ትንበያ ጥናት</u> | | |
| 1.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/1995 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/1995 | ሐምሌ 25 /1995 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1995 | ነሐሴ 25/1995 |
| 1.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 2/1995 | መስከረም 25/1996 |
| 1.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | መስከረም 26/1996 | ጥቅምት 5/1996 |
| 1.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ጥቅምት 6/1996 | ጥቅምት 20/1996 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ጥቅምት 10/1996 | ጥቅምት 25/1996 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ጥቅምት 15/1996 | ጥቅምት 27/1996 |
| | - ታቡሌሽን | ጥቅምት 28/1996 | ኅዳር 10/1996 |
| 1.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ጥቅምት 20/1996 | ኅዳር 20/1996 |
| 2 | <u>የግብርና ናሙና ጥናት በዋናው መኸር</u> | | |
| 2.1 | የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት | | |
| 2.2 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/1995 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/1995 | ሐምሌ 25 /1995 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 27/1995 | ነሐሴ 25/1995 |
| 2.3 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 2/1995 | የካቲት 10/1996 |
| 2.4 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ታህሣሥ 1/1996 | የካቲት 20/1996 |
| 2.5 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ታህሣሥ 10/1996 | ታህሣሥ 11/1996 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ታህሣሥ 20/1996 | መጋቢት 10/1996 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ጥር 15/1996 | መጋቢት 10/1996 |
| | - ታቡሌሽን | የካቲት 1/1996 | መጋቢት 20/1996 |
| 2.6 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ጥር 15/1996 | መጋቢት 30/1996 |

# የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር

የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚጀመርበት | ሥራው የሚጠናቀቅበት |
|---|---|---|---|
| 3 | የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት | | |
| | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/1995 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/1995 | ሐምሌ 25/1995 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ምምሪት | ነሐሴ 1/1995 | ነሐሴ 25/1995 |
| 3.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 2/1995 | ኅዳር 30/96 |
| 3.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ታህሣሥ 1/1996 | ታህሣሥ 10/96 |
| 3.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ታህሣሥ 5/1996 | ታህሣሥ 1/96 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ታህሣሥ 15/1996 | ጥር 5/96 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ታህሣሥ 20/1996 | ጥር 10/96 |
| 3.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ታህሣሥ 15/1996 | መጋቢት 30/96 |
| 4. | የመሬት አጠቃቀም ጥናት | | |
| 4.1 | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/1995 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/95 | ሐምሌ 25/95 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ስልጠና በዋናው መ/ቤት | ነሐሴ 1/1995 | ነሐሴ 25/1995 |
| 4.2 | መረጃ መሰብሰብ | ነሐሴ 27/1995 | ኅዳር 30/96 |
| 4.3 | ዶክመንቶች ወደ ዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ታህሣሥ 1/1996 | ታህሣሥ 10/96 |
| 4.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ታህሣሥ 5/1996 | ታህሣሥ 30/96 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ታህሣሥ 15/1996 | ጥር 5/96 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ታህሣሥ 20/1996 | ጥር 20/96 |
| | - ታቡሌሽን | ጥር 1/1996 | ጥር 20/96 |
| 4.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ታህሣሥ 15/1996 | መጋቢት 30/96 |
| 5 | የቤት እንስሳት ናሙና ጥናት | | |
| 5.1 | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/1995 |
| | የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/95 | ሐምሌ 25/95 |
| | የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ምምሪት | ነሐሴ 1/95 | ነሐሴ 25/95 |

# የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚጀመርበት | የቀጠለ ሥራው የሚጠናቀቅበት |
|---|---|---|---|
| 5.2 | የመረጃ መሰብሰብ | የካቲት 1/1996 | የካቲት 10/1996 |
| 5.3 | ዶክመንት ወደ ዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | የካቲት 15/1996 | የካቲት 20/1996 |
| 5.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | መጋቢት 2/1996 | መጋቢት 30/96 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | መጋቢት 10/96 | ሚያዝያ 10/96 |
| | - የዳታ ክሊኒንግና የቅንብር ሥራ | መጋቢት 25/96 | ሚያዝያ 15/96 |
| | - ታቡሌሽን | መጋቢት 25/96 | ሚያዝያ 20/96 |
| 5.6 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | የካቲት 15/96 | ሚያዝያ 30/96 |
| 6. | የግብርና ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | | |
| 6.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/95 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/1995 | ሐምሌ 25/1995 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1995 | ነሐሴ 25/1995 |
| 6.2 | መረጃ መሰብሰብ | መጋቢት 1/96 | ግንቦት 30/96 |
| 6.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ሰኔ 5/96 | ሰኔ 10/96 |
| 6.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ሰኔ 10/1996 | ሰኔ 25/96 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ሰኔ 15/1996 | ሐምሌ 5/96 |
| | - የዳታ ክሊኒንግና የቅንብር ሥራ | ሰኔ 20/1996 | ሐምሌ 15/96 |
| | - ታቡሌሽን | ጥር 1/1996 | ሐምሌ 30/96 |
| 6.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ሐምሌ 1/1996 | ሐምሌ 30/96 |
| 7 | የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት | | |
| 7.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1995 | ሐምሌ 10/95 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 10/1995 | ሐምሌ 25/95 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1995 | ነሐሴ 25/95 |
| 7.2 | መረጃ መሰብሰብ | ግንቦት 1/1996 | ግንቦት 30/96 |
| 7.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ሰኔ 5/1996 | ሰኔ 10/96 |
| 7.5 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ሰኔ 27/1996 | ሐምሌ 15/96 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ሐምሌ 20/1996 | ሐምሌ 25/96 |
| | - የዳታ ክሊኒንግና | ሐምሌ 20/1996 | ሐምሌ 25/96 |
| | - ታቡሌሽን | ሐምሌ 25/1996 | ነሐሴ 5/96 |
| 7.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ሐምሌ 1/1996 | ነሐሴ 10/96 |

# የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር

የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚጀመርበት | ሥራው የሚጠናቀቅበት |
|---|---|---|---|
| 8 | የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት | | |
| | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 1/1995 | ሰኔ 30/1995 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ሐምሌ 15/1995 | ሐምሌ 30/1995 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1995 | ነሐሴ 10/1995 |
| 8.2 | መረጃ መሰብሰብ | ወር በገባ በመጀመሪያ ቀን | በወሩ መጨረሻ |
| 8.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | የየወሩ መረጃ በቀጣዩ ወር 16ኛው ቀን | የየወሩ መረጃ በቀጣዩ ወር መጨረሻ ቀን |
| 8.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የዳታ ክሊኒንግና የቅንብር ሥራ | በወሩ መጀመሪያ ቀን | በ3ኛው ወር መጨረሻ ቀን |
| 8.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | የየወሩ መረጃ በ4ኛው ወር በመጀመሪያው ቀን | የየወሩ መረጃ በ4ኛው ወር በአምስተኛው ቀን |
| 9 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | | |
| | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 1/1995 | ግንቦት 30/1995 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ሰኔ 14/1995 | ሰኔ 22/1995 |
| 9.2 | መረጃ መሰብሰብ | እ.አ.አ. ወር በገባ በመጀመሪያ ቀን | እ.አ.አ. ወር በገባ በአስራ አምስተኛው ቀን |
| 9.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | በጥናቱ ወር በ28ኛው ቀን | በጥናቱ ወር የመጨረሻው ቀን |
| 9.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የዳታ ክሊኒንግና የቅንብር ሥራ | የየወሩ መረጃ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያው ቀን | የየወሩ መረጃ በ3ኛው ወር የመጨረሻ ቀን |
| 9.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | የየወሩ መረጃ በ3ኛው ወር በ16ኛው ቀን | የየወሩ መረጃ በ3ኛው ወር የመጨረሻ ቀን |

## የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር

የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት | ሥራው የሚጀመርበት | ሥራው የሚጠናቀቅበት |
|---|---|---|---|
| 10 | የወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት | | |
| 10.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ሚያዝያ 30 /1995 | መስከረም 14/1995 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ጥቅምት 14/1995 | መስከረም 18/1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ጥቅምት 19/1996 | መስከረም 27/1996 |
| 10.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጥቅምት 28/1996 | ጥቅምት 30/1996 |
| 10.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ኅዳር 3/1996 | ኅዳር 10/1996 |
| 10.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ኅዳር 10/1996 | ታህሣስ 10/1996 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ኅዳር 20/1996 | ታህሣስ 30/1996 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ኅዳር 30/1996 | ጥር 10/1996 |
| | - ታቡሌሽን | ጥር 1/1996 | የካቲት 30/1996 |
| 10.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ጥር 1/1996 | ሚያዝያ 30/1996 |
| 11 | የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | | |
| 11.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ጥቅምት 1/1996 | ጥር 23/1996 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | ጥር 26/1996 | የካቲት 30/1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | መጋቢት 4/1996 | መጋቢት 18/1996 |
| 11.2 | መረጃ መሰብሰብ | መጋቢት 23/1996 | ግንቦት 6/1996 |
| 11.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | ግንቦት 7/1996 | ግንቦት 12/1996 |
| 11.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ግንቦት 13/1996 | ሰኔ 5/1996 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ሰኔ 6/1996 | ሰኔ 20/1996 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ሰኔ 21/1996 | ሐምሌ 20/1996 |
| 11.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ሐምሌ 21/1996 | ነሐሴ 20/1996 |

## የ1996 የጥናቶች መርሃ-ግብር

የቀጠለ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12 | የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራች ዋጋ ሙከራ ጥናት | | |
| | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | መስከረም 1/1996 | ጥር 30/1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | የካቲት 20/1996 | የካቲት 26/1996 |
| 12.2 | መረጃ መሰብሰብ | መጋቢት 16/1996 | መጋቢት 30/1996 |
| 12.3 | የመረጃ ማጠናቀርና ማዘጋጀት | ሚያዝያ 10/1996 | ሰኔ 30/1996 |
| 13 | የኢኮኖሚ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ | | |
| 13.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ጥቅምት 1/1995 | ታህሣስ 30/1996 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መ/ቤት | የካቲት 1/1996 | የካቲት 5/1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | የካቲት 7/1996 | የካቲት 14/1996 |
| 13.2 | መረጃ መሰብሰብ | የካቲት 15/1996 | መጋቢት 20/1996 |
| 13.3 | ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት ማሰባሰብ | መጋቢት 21/1996 | መጋቢት 25/1996 |
| 13.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | መጋቢት 26/1996 | ሚያዝያ 26/1996 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ሚያዝያ 27/1996 | ግንቦት 10/1996 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ግንቦት 10/1996 | ግንቦት 20/1996 |
| | - ታቡሌሽን | ግንቦት 21/1996 | ግንቦት 30/1996 |
| 13.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ሰኔ 1/1996 | ሰኔ 30/1996 |

# የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1996 በጀት ዓመት መርሃ-ግብር

ሠንጠረዥ 3

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት/የጥናቱ መጠሪያ | መለኪያ | እስከ 1995 በጀት ዓመት የተከናወነ | የ1996 በጀት ዓመት ግብ | ወርሃዊ ስርጭት ሐ | ነ | መ | ጥ | ኅ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | ወደ 1997 የሚሸጋገር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | **የዝግጅት ሥራ** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.2 | የሰብል ሁኔታ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ጥናት | % | - | 15.0 | 8.18 | 6.82 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.3 | የቋሚ ሰብሎች፣ አትክልትና ሥራ ሥር | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተክሎች ውጤት ሙከራ ጥናት | % | - | 15.0 | - | - | 15.0 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት | % | - | | | | | | | | | | | | | | |
| | - የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የመሬት አጠቃቀም | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የቤት እንስሣት ናሙና ጥናት | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.4.1 | የግብርና ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.4.2 | የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት | % | 6.75 | 8.25 | 4.50 | 3.75 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.4.3 | የግብርና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች * | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | - የሶማሌ ብሔራዊ ክልል እንስሳት ቆጠራ | % | - | 15.00 | - | - | - | 15.0 | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የአፋር ብሔራዊ ክልል እንስሳት ቆጠራ | % | - | 15.00 | - | - | - | 15.0 | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.5 | የ1995 የተሻልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ.ጥናት | % | - | 15.00 | - | - | - | - | - | 3.75 | 3.75 | 3.75 | 3.75 | - | - | - | - |
| 1.6 | የኢኮኖሚ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ | % | - | 15.00 | 2.01 | 2.01 | 2.01 | 2.01 | 2.01 | 2.01 | 2.01 | 0.93 | - | - | - | - | - |
| 1.7 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | % | 15.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.8 | የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት | % | 9.00 | 6.00 | 2.50 | 2.50 | 1.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 1.9 | ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት | % | 6.00 | 9.00 | 3.00 | 3.00 | 3.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 2. | **መረጃ መሰብሰብ** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | % | - | 45.00 | - | - | 45.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 2.2 | የሰብል ሁኔታ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ጥናት | % | - | 45.00 | - | - | 45.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 2.3 | የቋሚ ሰብሎች፣ አትክልትና ሥራ ሥር | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተክሎች ውጤት ሙከራ ጥናት | % | - | 45.00 | - | - | - | 9.00 | 9.00 | 9.00 | 9.00 | 9.00 | - | - | - | - | - |
| 2.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | - የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን | % | - | 45.00 | - | - | 8.44 | 8.44 | 8.44 | 8.44 | 8.44 | 2.80 | - | - | - | - | - |
| | - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | % | - | 45.00 | - | - | 15.00 | 15.00 | 15.00 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የመሬት አጠቃቀም | % | - | 45.00 | - | - | 19.30 | 19.30 | 6.40 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የቤት እንስሣት ናሙና ጥናት | % | - | 45.00 | - | - | - | - | - | - | - | 45.00 | - | - | - | - | - |

* ለቆጠራው ከመንግሥት በጀት ከተመደበ የቆጠራው ሥራ ይካሄዳል።

| ተ.ቁ | የሥራው ዓይነት/የጥናቱ መጠሪያ | መለኪያ | እስከ 1995 በጀት ዓመት የተከናወነ | የ1996 በጀት ዓመት ግብ | ወርሃዊ ስርጭት | | | | | | | | | | | | ወደ 1997 የሚሸጋገር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ሐ | ነ | መ | ጥ | ኅ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| 3.8 | የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት | % | - | 5.00 | - | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.45 | 0.50 | - |
| 3.9 | ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት | % | - | 5.00 | - | - | - | - | 2.50 | - | - | - | - | 2.50 | - | - | - |
| 4. | **መረጃ ቅንብር** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | - | 17.65 | 7.35 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 4.2 | የሰብል ሁኔታ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 4.3 | የቋሚ ሰብሎች፣ አትክልትና ሥራ ሥር | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ተክሎች ውጤት መከራ ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | 25.00 | - | - | - | - |
| 4.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | - የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | 5.00 | 7.50 | 7.50 | 5.00 | - | - | - | - |
| | - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | 13.89 | 11.11 | - | - | - | - | - | - |
| | - የመሬት አጠቃቀም | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | 13.89 | 11.11 | - | - | - | - | - | - |
| | - የቤት እንስሣት ናሙና ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | 8.33 | 16.67 | - | - | - | - |
| 4.4.1 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 10.00 | 15.00 |
| 4.4.2 | የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 25.00 |
| 4.4.3 | የግብርና ቆጠራ ቀሪ ሥራዎች * | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | - የሶማሌ ብሔራዊ ክልል እንስሳት ቆጠራ | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | 25.0 | - | - | - | - | - | - | - |
| | - የአፋር ብሔራዊ ክልል እንስሳት ቆጠራ | % | - | 25.00 | - | - | - | - | 7.14 | 17.86 | - | - | - | - | - | - | - |
| 4.5 | የ1995 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ.ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 10.00 | 15.00 |
| 4.6 | የኢኮኖሚ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ | % | - | 25.00 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 10.00 | 15.00 |
| 4.7 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | % | - | 25.00 | 0.68 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.22 | 2.12 | - |
| 4.8 | የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | 2.50 | - |
| 4.9 | ወቅታዊ የሥራ ሁኔታ ጥናት | % | - | 25.00 | - | - | - | - | 5.00 | 7.50 | - | - | - | 5.00 | 7.50 | - | - |
| 5. | **ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት** | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | % | - | 10.00 | - | - | - | 3.33 | 6.67 | - | - | - | - | - | - | - | - |
| 5.2 | የሰብል ሁኔታ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ጥናት | % | - | 10.00 | - | - | - | 10.0 | - | - | - | - | - | - | - | - | - |

## 10. ትኩረትና መመሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

በ1996 በጀት ዓመት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ላቀዳቸው ጥናቶች ተግባራዊነት መ/ቤቱ የራሱን ዝግጅቶች እያከናወነ ሲሆን፣ ያቀደውን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችል በበላይ አካል ትኩረት ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ፦

ሀ/ የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1996 በጀት ዓመት ለማከናወን ያቀዳቸው ጥናቶች በአምስት ዓመቱ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም ላይ የተያዙ ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህን ጥናቶች ለማጥናት ለበጀት ዓመቱ የካፒታል በጀት ጣሪያ የሚደለደልበት ወቅት የተሰጠን በጀት አነስተኛ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ በፕሮግራሙ ላይ የተያዙት ጥናቶች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ በዝርዝር የበጀት ጥያቄው ላይ የቀረበው በጀት እንዲፈቀድ በበላይ አካል በኩል ትኩረት ማግኘት አለበት፣

ለ/ መ/ቤቱ አሁን ያለበት ቢሮ ቀደም ብሎ ለነበረው የሰው ኃይልና ሎጂስቲክስ በቂ ነበር፡፡ ነገር ግን በየጊዜው የመ/ቤቱ መዋቅር እየተሻሻለና እያደገ የመጣ በመሆኑ በቂና ተስማሚ ቢሮ ማግኘት ወሣኝ እየሆነ መጥቷል፡፡ ስለዚህ መ/ቤቱ በቂ ቢሮ ለማግኘት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉም የሚመለከታቸው ክፍሎች ከጎኑ ሆነው ድጋፍ እንዲሰጡት ይጠይቃል፡፡